የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.16
ADDIS ABABA 28th December, 2004


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፩/፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ለግብርና ዘርፍ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.... ገጽ. ፪ሺ፱፻፹፫


**CONTENTS**


**Proclamation No. 4 31/2004**

The African Development Fund Loan Agreement for Financing the Agriculture Sector Support Project Ratification Proclamation……. Page. 2983


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፩/፲፱፻፺፯

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለግብርና ዘርፍ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ዩ.ኤ. ፳፩ሚሊዮን፪፻፵ሺ (ሃያ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ ፲፪ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም ዐቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 431/2004.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of twenty one million two hundred and forty thousand Units of Account (UA 21,240,000) for financing part of the Agriculture Sector Support Project, was signed on the 12th day of February, 2004;

**WHEREAS,** basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of December, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለግብርና ዘርፍ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ስለመፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፩/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ፌብራሪ ፲፪ ቀን ፪ሺ፬ የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩኤ. ፳፩ሚሊዮን፪፻፵ሺ (ሃያ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ 19 ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ 19 ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The African Development Fund Loan Agreement for Financing the Agriculture Sector Support Project Ratification Proclamation No. 431/2004."

## 2. Definition

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund on the 12th day of February 2004.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of twenty one million two hundred forty thousand Units of Account (UA 21,240,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 28th day of December, 2004.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of December, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**